# ደንብ

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፦ COB-RA, COC-RA, COF-EA, COF-RA, GDD-RA, IGN, IJA-RA, JFA-RA, JGA-RB, JGA-RC, JGB-RA, JPC-RA, JPD-RC

ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦ Office of School Support and Well-being; Office of the School System Medical Officer; Office of the Chief Operating Officer

## የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ እና ሌሎች ተማሪዎችን ስለሚመለከቱ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መመሪያ

I. **ዓላማ**

ተማሪዎችን የሚመለከቱ የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆች የመጠቀምና ማጬስ ክስተቶችን የአፈጻፀም ሂደት ለመመስረት

II. **ትርጓሜ**

A. እጽበሜሪላንድ ህግ በበሜሪላንድ ቁጥጥር ስር ያለ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ህግ፣በሀኪም የታዘዘ መድሃኒት ወይም የኬሚካል ንጥረ ነገር ላልተፈለገ እና ጎጂ ዓላማዎች በሚውልበት ጊዜ ቁጥጥር የሚደረግበት አደገኛ ንጥረ ነገር ተብሎ ይገለጻል።

B. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት ማንኛውም MCPS የሚያካሄደው ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም፣MCPS የሚገለገልባቸው የት/ቤት አውቶቡሶች እና ሌሎች MCPS የሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች፣ MCPS የተያዘ ወይም የሚሰራ ፋሲሊቲ እና/ወይም ግቢን ጨምሮ ማንኛውም ተማሪዎችን በማሳተፍ MCPS የሚተገብራቸው እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ንብረት ነው።

C. ማጨስ ማለት ማንኛውንም የተለኮሰ ሲጋራ፣ ሲጋራ፣ ትንባሆ ወይም ሌላ ማንኛውንም የትምባሆ ምርት መጠቀም ወይም መያዝ ማለት ነው። ይህ ከማጨስ ጋር የሚመሣሰል ማንኛውንም አይነት መሳሪያዎችን ያካትታል።

III. **የአፈጻፀም ቅደም-ተከተል**

A. የተከለከለ የተማሪ አጠቃቀም

1. ተማሪዎች፦ 21 ዓመት እድሜ ያላቸው እና ከዚያ በላይ የሆኑ ተማሪዎችን ጨምሮ፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ከ 21 አመት እድሜ በታች የሆኑ ግለሰቦች ከመጠቀም ክልከላ የተደረጉባቸው በሜሪላንድ በህጋዊ መንገድ መጠቀም የማይቻሉ ምርቶች ናቸው። በዚህ ባይወሰንም ይህ የሚያጠቃልለው—

a) የአልኮል መጠጥ፣

b) ትምባሆ (የኒኮቲን ይዘቱ ምንም ይሁን ምን፣ የኤሌክትሮኒክስ ማጨሻ መሳሪያዎችን እና በውስጣቸው የሚገኙ ፈሳሾችን ጨምሮ) እና መለዋወጫዎችን እና የመለዋወጫ እቃዎችን ጨምሮ፣ እና

c) በሜሪላንድ ህግ እንደተገለጸው ካናቢስ፣ ካናቢስ በውስጡ ያለበት ነገር፣ የካናቢስ ምርቶች ወይም ካናቢስ-የተጨመሩባቸው ምርቶች ናቸው።

2. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ "MCPS Regulation JPC-RA" ላይ ከተገለጹት የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች በስተቀር ስለ ተማሪዎች የመድሃኒት አያያዝ ለተማሪዎች መድሃኒቶችን መያዝ የተከለከለ ነው። በምንም አይነት ሁኔታ ተማሪዎች ካናቢስን ለህክምና አገልግሎት ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች፣ መፍዘዝ/ከፍተኛ የእንቅስቃሴ መዛባት አበረታች መድሀኒቶችን ጨምሮ እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም።

3. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ "MCPS Regulation JPD-RC" ላይ እንደተገለጸው፣ "Opioid" ኦፒዮይድ ከመጠን በላይ የመውሰድ ምልክት ለሚታይባቸው ግለሰቦች የድንገተኛ ህክምና እርዳታ፣ "naloxone" ናሎክሰንን MCPS ንብረት እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ ተግባራት ላይ ተማሪዎች ናሎክሰን/naloxone በመያዛቸው ምክንያት ብቻ የዲሲፕሊን እርምጃ አይወሰድባቸውም። ተማሪዎች ከመጠን በላይ ኦፒዮይድ የወሰደ(ች) ተማሪ ሲመለከቱ ከተጠራጠሩ፣ እርዳታ እንዲያገኙ DHHS ወይም MCPS ሰራተኞችን መጠየቅ እና/ወይም 911 እንዲደውሉ አጥብቀን እናበረታታለን።

B. መገናኛ

በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ፣ ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣MCPS ደንቦች እና ከአልኮል፣ ከካናቢስ፣ ከትምባሆ እና ከሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው መድሃኒቶች እና ከሲጋራ ማጨስ ነጻ የሆነ ለማስተማር፣ ለመማር እና ለመስራት ምቹ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር የተነደፉ ተዛማጅ ህጎች በጽሁፍ ይገለጽላቸዋል።

C. መታወቂያ እና እርዳታ

1. በተማሪው(ዋ) መምህር አስተያየትና ግምት አንድ ተማሪ ከጤና ጋር የተገናኙ ምልክቶችን እያሳየ(ች) ከሆነ ወይም በክፍል ውስጥ በትክክል መስራት ካልቻለ(ች) ተማሪው(ዋ) ወደ ት/ቤት ጤና ክሊኒክ ሪፈራል የመላክ ሂደቶችን ይከተላሉ እና ርእሰመምህሩ እንዲያውቁት ይደረጋል።

2. ከአስተማሪ፣ ከካውንስለር፣ ከርእሰ መምህር ወይም ከሌላ ሙያዊ አስተማሪ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግሮችን እንዴት መቋቋምና ማሸነፍ እንደሚቻል መረጃ ወይም ምክር ለሚፈልግ ተማሪ የስቴቱ ህግ አንዳንድ ጥበቃዎችን ይሰጣል። በእንደዚህ ዓይነት የተገኘ የካውንስሊንግ/የምክር ወይም የመረጃ ክፍለ ጊዜ ላይ የተገኙ መረጃዎች በማንኛውም ሁኔታ ይፋ ሳይደረጉ በሚስጥር ይጠበቃሉ።

3. ተማሪው(ዋ) በተገቢው ጊዜ ሁሉ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች እርዳታ እንዲ(ድት)ጠይቅ ማበረታታት ያስፈልጋል።በአስተማሪው ግምገማና አስተሳሰብ፣ የተማሪው(ዋ) አእምሮአዊ ወይም አካላዊ ጤንነት በአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ምክንያት ለአስጊ ሁኔታ የተጋለጠ ካልሆነ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን የማሳተፍ ውሳኔ በተማሪው(ዋ) እና በአስተማሪው(ዋ) በጋራ ተነጋግረውና ተስማምተው ሊሆን ይገባል።እንደዚህ አይነት አደጋ ከደረሰ፣ርእሰመምህሩ፣ወላጆች እና/ወይም አሳዳጊዎች፣ እና የት/ቤቱ የማህበረሰብ ጤና ጠባቂ ነርስ/ቴክኒሻን ተገቢውን የህክምና እርምጃ እንዲወስዱ ስለሁኔታው ማወቅ አለባቸው።

D. ሪፖርት ማድረግ

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውስጥ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ ወይም ሌላ አደንዛዥ እፅ እና የተከለከለ መድሃኒት መጠቀም፣ ማጨስ፣ መያዝ፣ ወይም ማከፋፈልን የሚመለከቱ ክስተቶች ለርዕሰ መምህር/ለዳይሬክተር ወይም ለተወካይ ሪፖርት መደረግ አለበት።

2. ርእሰ መምህሩ/ዳይሬክተሩ ወይም ተወካይ የህግ ጥሰት ሊኖር ይችላል ብለው የሚጠረጥሩበት ምክንያታዊ ሁኔታ ካላቸው፣ እንደ ከባድ ክስተት ይቆጠራል፣ MCPS Regulation COB-RA ክስተትን ሪፖርት ማድረግድንጋጌ መሠረት የተቀመጡትን ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው። እና እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ለሚመለከታቸው MCPS ቢሮዎች፣ የህግ አስከባሪ አካላት ወይም የድንገተኛ አደጋ አገልግሎት ሰጪዎች ማሳወቅ፤ ክስተቱን ሪፖርት ማድረግ፣ እና መረጃ መስጠት አለበት።

E. አጠራጣሪ ቁሳቁሶችን መፈተሽና መያዝ

ን

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የተማሪ ንብረት ፍተሻን በሚመለከቱ ማንኛቸውም ጥያቄዎች፥ ለስርአት አቀፍ የደህንነት እና ድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ቢሮ (OSSEM) እና/ወይም "MCPS Regulation JGB-RA" ፍተሻ እና ቁጥጥር ስር ስለማድረግ እንዲያማክሩ እናስገነዝባለን። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ አልኮል፣ ካናቢስ ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት መድሃኒት ነው ብለው የሚጠረጥሩት ንጥረ ነገር ይዞ(ዛ) ከተገኘ(ች)፣ የእቃው አያያዝ በሚከተለው መንገድ መሆን አለበት።

1. OSSEM ላይ እንደተገለፀው ተገቢ የደህንነት ጥንቃቄዎችን በመከተል ንብረቱ በፖስታ ውስጥ ወይም በሌላ መንገድ መታሸግ አለበት።

2. እንዴት እንደተገኘ ቀኑ፣ ሰዓቱ እና አይነቱ በመያዣው ላይ ተጠቁሟል። ነገር ግን፥ ከተማሪ(ዋ) እጁ የተገኘው የእፅ አጠቃቀም ካውንስሊንግ መረጃ የሚሰጥበት ኮንፈረንስ ወቅት ከሆነ፣ የተጠረጠረው ዕፅ የተገኘበ(ባ)ት ተማሪ ስም አይገለጽም።

3. የተጠረጠሩት ንጥረ ነገሮች MOU-CEO እና MCPS Regulation COB-RA፣ ክስተትን ሪፖርት ማድረግ የተቀመጡትን ሂደቶች በመከተል ወደ ርእሰመምህር/ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ይተላለፋል። MOU-CEO የሕግ አስከባሪ አካላት በምርመራው ሂደት ግንባር ቀደም መሆን እንዳለባቸው ያረጋግጣሉ–

    (1) ማሰራጨት ወይም ማምረት፣ ወይም

    (2) ይዞ መገኘት፣ ወይም

    (3) ቁጥጥር የሚደረግበትን አደገኛ ንጥረ ነገር ለማሰራጨት በማሰብ ይዞ መገኘት።

4. ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤቱ ደኅንነት ላይ ከባድ አደጋን የሚፈጥር ንጥረ ነገር ይዞ መገኘት ወይም ለግል ጥቅም ከሚበቃ በላይ ይዞ መገኘት የተማሪ ስነምግባር ደንብ /Student Code of Conduct in MCPS ላይ የተመለከተውን የዲሲፕሊን እርምጃ ከፍ ለማድረግ እንደ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ይህ ንጥረ ነገር በትምህርት ቤቱ ደኅንነት ላይ ከፍተኛ ስጋት የሚፈጥር መሆኑን ወይም ለግል ጥቅም ከሚይዙት በላይ መሆኑን ለማወቅ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር መማከር ይችላል/ትችላለች (የውጭ ባለሙያዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።)

F. የሚያስከትለው መዘዝ

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግበት መድሃኒት/እፅ ይዘው የተገኙ፣ የተጠቀሙ ወይም የሚያሰራጩ ተማሪዎች MCPS የተማሪ የስነምግባር ደንብ መሰረት የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

2. ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ወይም በት/ቤት በሚደገፉ ቡድኖች ውስጥ የመሪነት ቦታዎችን ለመያዝ ተማሪው(ዋ) ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ውጭ በሌሎችም ቦታዎች ከአልኮል፣ ከካናቢስ፣ከትምባሆ ወይም ሌላ አደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ነፃ የመሆን ተጨማሪ ገደቦችን እና የሚያስከትሉ መዘዞችን ለመቀበል ስምምነት እንዲ(ድት)ገባ ሊጠየቅ ይችላል/ልትጠየቅ ትችላለች።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** አባሪ የሜሪላንድ ኮድ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀፅ §5-101, §5-602, §5-602, §5-624, እና 5-627(a); ስለ ትምህርት አንቀፅ §7-412 እና § 26-103; አጠቃላይ ጤና አጠባበቅ-አንቀፅ §8-101 (i); አልኮል መጠጦች እና ካናቢስ አንቀፅ፤ የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ 09.12.23.01

**የደንቡ ታሪክ፡**የቀድሞው MCPS ደንብ ቁጥር. 285-10 ዲሴምበር 29, 1976 ኦክቶበር 1986 ተሻሽሏል። ዲሴምበር 19, 2013 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 11, 2014 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 19፣ 2023 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳሰለ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org